የሰ/መ/ቁ. 26262

ኅዳር 3/2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ዋጋዬ ገብሬ ጠበቃ አዝመራ ነጋሽ

ተጠሪ፡- አቶ ደመላሽ ታምሩ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ለተጠሪ የተሰጠው የወራሽነት ማስረጃ በአግባቡ ስላልሆነ ውሣኔው ይሰረዝልን በማለት አመልካቾች ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ በየደረጃው ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ ሟች እናቴ ወ/ሮ እታገኝ ገብሬ ስለሞቱ ወራሽነቴ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቦ ፍ/ቤቱም የአመልካችን ምስክሮች ሰምቶ የሟች ወ/ሮ እታገኝ ገብሬ ወራሽ ነው በማለት ውሣኔ ከሰጠ በኂላ የአሁን አመልካቾች ሟች ወ/ሮ እታገኝ ገብሬ እህታቸው እንደሆኑና ልጅም ያልወለዱ መካን የነበሩ መሆናቸውን ገልጸው ተጠሪ የሟች እህታችን ወራሽ ነው ተብሎ ማስረጃ እንዲያገኝ የተሰጠው ውሣኔ መብታችንን የነካ ስለሆነ ይሄው ውሣኔ ሊሰረዝልን ይገባል በማለት ውሣኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ቀደም ሲል የሟች ወራሽነቱን ባረጋገጠ ጊዜ የተሰሙትን ምስክሮች በድጋሚ አስቀርቦ የምስክርነት ቃላቸውን ከሰማ በኂላ አመልካች

/የአሁን ተጠሪ/ ሚች ወ/ሮ እታገኝ ገብሬ የወለዱት ልጅ ወይንም የጉዲፈቻ ልጅ ስለመሆኑ በምስክሮች ስላልተገለጸ ልጅ ነው አይደለም የሚለው ጭብጥ የፍ/ቤቱ ሥልጣን ስላልሆነ አመልካቾች በቅድሚያ በዚህ ነጥብ ላይ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው አረጋግጠው ሲመጡ ወራሽነትን አስመልክቶ የቀረበው አቤቱታ የሚታይ ነው በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኙን ያልተቀበለው ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱም መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የቀረበው አቤቱታ መርምሮ አመልካቾች የተጠሪ ወራሽነት የተረጋገጠበትን ውሣኔ በመቃወም ባቀረቡት አቤቱታ ላይ የአ/አ ከተማ ነክ ፍ/ቤት የሰጠውና በይግባኝ የጸናው ትዕዛዝ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 አኳያ ለሰበር ቀርቦ የሚጣራ ሆኖ በማግኘቱ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ነጥብ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ የሚች ወ/ሮ እታገኝ ገብሬ ልጅ ስለሆንኩ የወራሽነት ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ለከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ባመለከተው መሠረት ፍ/ቤቱ ለተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ሠጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካቾች ተጠሪ የሚች እህታችን እታገኝ ገብሬ ልጅ አይደለም ሚችም ልጅ ያልወለደችና መሃን ስለነበረች ፍ/ቤቱ ተጠሪ የሚች ወራሽ ነው በማለት ማስረጃ እንዲሰጠው የሰጠው ውሣኔ መብታችንን የነካ ስለሆነ ይሄው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በአንድ ክርክር ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንደዚሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው መቃወሚያ ማቅረብ እንደሚችል በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 ላይ ተመልክቷል፡፡

የዚህ ዓይነት አቤቱታ ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜም ፍ/ቤቱ ሊይዘው የሚገባ የክርክር ጭብጥ አስቀድሞ የተሰጠው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለውን ነው፡፡ በዚህም መሠረት የአ.አበባ ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ይህንኑ ጭብጥ ይዞ በአንድ በኩል ተጠሪ የሟች ልጅ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ በሌላም በኩል አመልካቾች ተጠሪ የሟች ልጅ ስላለመሆኑ በበኩላቸው ያቀረቡትን ማስረጃ መዝኖ በጭብጥ በተያዘው ላይ ዕልባት መስጠት ሲገባው በልጅነት ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት ከፍ/ቤቱ የሥረ-ነገር ሥልጣን ውጪ ስለሆነ አመልካቾች በቅድሚያ በልጅነት ክርክሩ ላይ ሥልጣን ባለው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አስወስነው መቅረብ አለባቸው በማለት ለጉዳዩ እልባት ሳይሰጥ መቅረቱ እንደዚሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትና ሰበር ችሎቱ ይህንኑ ጉልህ የሆነ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ሳያርሙ መቅረታቸው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአ/አበባ ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.1537/95 በ21/01/97 የሰጠው ትዕዛዝ፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01785 በ30/9/97 የሰጠው ውሣኔና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 02604 በ9/4/98 የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት መቃወሚያ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ተመርምሮ ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባ ስለሆነ የአ.አ. ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በዚሁ መሠረት መርምሮ እንዲወስን ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

ነ/ዓ